# አንቀፅ 39 ከፖለቲካ ምህዳሩ አንፃር ሲቃኝ!

**ከሃብሮማይ**
ghabrom@yahoo.com

አንድ ሰው ፀሎት ወደ ፈጣሪ እያደረሰ ነበር፡፡ፀሎቱ ፈጣሪውን ዘንድ ተሰማለትና ፈጣሪን እንዲህ ብሎ ጠየቀው፡፡አንተ የምትፈልገው ንገረኝና የፈለግከውን ልስጥህ ያንተን እጥፍ ደግሞ ለጓደኛህ ልስጥ አለው፡፡ ሰውየው ስስታም ነበርና ጓደኛየ ከኔ በላይ ሊሆንማ አይገባም ብሎ አሰበ ለፈጣሪም እንዲህ አለው፡፡ ፈጣሪዬ ከሁለቱ ዓይኔ አንዷን አጥፋልኝ ለጓደኛዬ ደግሞ እጥፍ ስለምትሰጠው ሁለቱን ዓይኑን አጥፋለት አለው ይባላል፡፡

የአገራችን ታሪክ መሰረቱ የብሄር ብሔረሰቦችና የሃይማኖት ብዙህነት ሆኖ ሳለ ፣በዚሁ ብዙህነት ላይ ተመስርቶ ይህንኑ ለማስተናገድና ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ስርአት ሳይኖረን ረዥም ዘመናት ኖረናል፡፡ ይህ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መፍትሄ ሳይበጅለት ቆይቶ በደርግ ውድቀት ዘመን አከባቢ የመበታተን አደጋው ጫፍ የደረሰበት ሁኔታ ተፈጥሮ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ይህ ክስተት ይንፀባረቅባቸው ከነበሩ ወቅቶች መካከል የሚነሳው የአጼዎቹ ዘመን ነው፡፡ ይህ የንጉሱ አገዛዝ ዘመን ብሄር፤ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የፊውዳል ቀንበር ተጭኖባቸው ለንጉስ እየገበሩ፣ለንጉስ እየሰሩ ብሔረሰባዊ ብዙህነትን እንደ ድክመት በመውሰድ በገዢዎች ተምሳሌት የተቀረጸ አንድ ወጥ ኢትዮጵያዊነት ለማስፈን የተቀናጀ ጥረት ይደረግበት ነበር፡፡

ደርግም የኢትዮጵያ ብሔር ፣ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች የነፃነት እንቅስቃሴ ተጠቅሞ ዘውዳዊውን ስርዓት አስወግዶ ስልጣን ላይ ወጥቶ ብዙህነትን አንድ ወጥ በሆነ ኢትዮጵያዊነት ፣በአንድ ፀረ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተምሳሌት በሚቀረጽ ኢትዮጵያዊነት ለመተካት የተደረገው ርብርብ እያደረ ቀውሱን አባብሶ

በደርግ መንግስት የመጨረሻ ዓመታት አከባቢ ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ለብተናና ለብሔሮች መናቆር የተጋለጠች አገር ሆና ነበር፡፡

ለዘመናት ስር እየሰደደና እየተወሳሰበ የመጣው ድህነት ከጦርነቱ ጋር እየተመጋገበ አገራችንን ወደ መጨረሻው የጥፋት ጠርዝ ላይ በደረሰበት ወቅት የተለያዩ የፖለቲካ ተንታኞች ከሌሎች የመበታተን አደጋ የደረሰባቸው አገሮች በማመሳሰል ክፉ ክፉውን ገምተው ነበር፡፡

ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን በመገንባት የጦርነቱን ፖለቲካዊ ምንጭ ማድረቅና ለልማት የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር ካልተቻለ ይህ ግምታቸው እውን መሆኑ በፍፁም የማይቀር ትንበያ ነበር፡፡የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ጉዳይ በአገራችን የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ህዝቡን ከአስከፊ እልቂት ፤አገሪቱን ከጠቅላላ ብተና የመታደግ ጉዳይም ጭምር መሆኑን የሚያረጋግጥ አጋጣሚ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ስለሆነም የህዝቡን ጥያቄ በመረዳትና አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት የብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች መብት እስከመገንጠል ያለምንም ገደብ በሕገመንግስቱ በማያሻማ መልኩ ተቀምጧል፡፡

የዴሞክራሲያችን መለያ ባህርያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ የብሄሮች፤ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ ነው፡፡ይህ መብት የህዝቦችን ወንድማማችነት በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ አንድነት ለመፍጠር ታቅዶ ነው፡፡

ስለሆነም አንድነታቸውም ሰፊ ግዛት በመያዝ አስፈላጊነት ላይ የተመሰረተ የተለያዩ ህዝቦች አስተዳደራዊ ትስስር ሳይሆን በጋራ ዓላማ!በጋራ እሴቶች ላይ የተመሰረተ አንድነት ነው፡፡ በዘር !በብሄር!ብሄረሰብ !በቀለምበፆታ ! !በቋንቋ !በሃይማኖትበ !ፖለቲካበ !ማህበራዊ አመጣጥ!በሃብት! በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና

የማግኘት መብት ተጎናፅፏል፡፡ በህገ መንግስቱ ህዝባችን የተጎናፀፈውን መብት በማያሻማ መልኩ ተግባራዊ በመደረጉ አሁን በተጨባጭ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ወደኋላ ሊቀለበስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

የብሄር ብሄረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚለውን ህዝቦች በፍላጎታቸው፤በመከባበርና በመፈቃቀር የሚኖርባትን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ የማይተካ ሚና አለው፡፡

የብሄር ብሄረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚለውን ቃል የሰፈረው አገራችን ለመበታተን ሳይሆን የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በመልካም ፍቃዳቸው በጋራ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ተመስርተው በልዩነታቸው ላይ አንድነት ፈጥረው የሚኖርባት ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ነው፡፡አሁን በተጨባጭ ህዝቦች በልዩነታቸው ውስጥ በመከባበር፤በመፈቃቀር፤በመልካም ፍቃድና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አንድነት ፈጥረው የሚኖርባት ኢትዮጵያ እውን ሆናለች፡፡

እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አንድነት መፍጠር የቻሉት አንዱን ብሄር ከሌላው ብሄር እኩል መብት ስለተጎናፀፈ፤ ማንኛውም ዜጋ በየትኛውን ክልል የመዘዋወር! የመኖርና የመስራት መብት ስላለው አንድ የሆነ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋፆ ስላለው ነው፡፡

ለአንድ ብሄር ቢመችህም ባይመችህም የኔ ጉዳይ አይደለም ብለህ በሃይል አስገድደህ አንድ እንሁን በማለት የመገንጠል መብቱን መንፈግ ማለት የፖለቲካ ምህዳሩን ጭራሹ መድፈን ማለት ነው፡፡ህዝቦች በፍላጎታቸውና መልካም ፍቃዳቸው አንድነት የሚፈጥሩበት ሁኔታ ከተመቻቸላቸው ግን በአገራቸው ሰፊ የሆነ የፖለቲካ ምህዳር እንዳለ የሚያረጋግጥ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በአገራችን ያለ ነገርም ይሄ ነው፡፡ህዝቦች በመልካም ፍቃዳቸው፤ በፍላጎታቸው እንዲሁም በጋራ ጥቅም ላይ ተመስርተው አንድነትን ፈጥረው እየኖሩ

ነው፡፡ይህን የሆነበት ምክንያት ደግሞ እስከ መገንጠል የሚደርስ ያልተገደበ መብት ስለተጋናፀፉ ነው፡፡ስለሆነም በአገራችን ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ሰፊ እንደሆነ የሚያረጋግጥ መሰረታዊ የዴሞክራሲ አካል ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

ታድያ! የአገራችን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚወሱንበትና እስከ መገንጠል የሚደርስ ያልተገደበ መብት ተጎናፅፈው ሳለ ይሄም የፖለቲካ ምህዳሩ ስፋት በማያሻማ መልኩ የሚያረጋግጥ መሆኑ ለቀባሪ እንደ ማርዳት መሆኑ እያወቁ ለምንድነው በአገራችን የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቧል እያሉ የሚደስኩርልን?

አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች አንቀፅ 39 እንደማይቀበሉት ፀሐይ የሞቀው ሐቅ ነው፡፡ሊቀበሉት ቀርቶ እስከ መገንጠል የሚል ያልተገደበ መብት መስማት ራሱ ሲያንገሸግሻቸው ነው የሚስተዋሉት፡፡ታድያ እነዚህ ተቃዋሚዎች ህዝቦች የፈለጉትን የመወሰን መብት ሲያጥላሉና እንዳለፉት ስርዓቶች ብሄር ብሄረሰቦች በሃይል ቀይጠው አንድ ወጥ ኢትዮጵያ ለመመስረት ማለማቸው ገና ከጅምራቸው አገሪቷ በማያላውስ የፖለቲካ ምህዳር ለመክተት ጥረት እያደረጉ መሆናቸው የሚያመላክት አይደለምን?

እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ለህዝቦች እስከ መገንጠል የሚደርስ ያልተገደበ መብት እንደ አንድ የዴሞክራሲ መሰረት አድርጎ ለሚቀበል መንግስት በአገራችን የፖለቲካ ምህዳሩ እያጠበበብን ነው ማለታቸው ከምን ይሆን?

ተቃዋሚዎች ነገ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አገር እንመራለን የሚል ራእይ ካላቸው በመጀመርያ መሰረታዊ ዓላማቸውን ሊፈትሹ ይገባል፡፡ለብሄር ብሄረሰቦች እስከመገንጠል የሚደርስ ያልተገደበ መብት ከሰጠናቸው አገራችን ትበታተናለች፡፡ስለዚህ ብሄር ብሄረሰቦችን መልካም ፍቃዳቸውን ሳንጠይቅ በሃይል እንቀይጣቸው፤አንድ እናድርጋቸው ብለው ማሰባቸው ራሱ ፀረ ዴሞክራሲና የፖለቲካ ምህዳሩን ጭራሽኑ የሚደፍን አስተሳሰብ አይደለምን?

የተለያዩ አገሮች በተለያየ አጋጣሚ አንድ የነበሩ አሁን ግን የተበታተኑ አሉ፡፡ለምሳሌ ያኸል ዩጎዝላቭያና ሩስያ መውሰድ ይቻላል፡፡እነዚህ አገራት እስከ መገንጠል የሚደርስ ያልተገደበ መብት በህገመንግስታቸው ውስጥ አልነበረም፡፡በህገመንግስታቸው ይሄን የመገንጠል መብት አላካተቱም ግን ተበታትነዋል፡፡የተበታተኑበት ምክንያት ብዙ ቢሆንም አንደኛውና ዋነኛው ግን ህዝቡ የፖለቲካ ምህዳሩ አላላውስ ስላለው ነበር፡፡ስለሆነም በሕገመንግስት የመገንጠል መብት ኖረ አልኖረ ህዝቦች በመልካም ፍቃድና በጋራ ጥቅም ላይ ያልተመሰረተ አንድነት ከፈጠሩ መበታተናቸው የማይቀር ነው፡፡ተቃዋሚዎች በሕገመንግስቱ እስከ መገንጠል የሚደርስ መብት ስለተሰጠ ህዝቦች ይበታተናሉ ብለው ማሰባቸውና እስከ መገንጠል የሚደርስ መብት መቃወማቸው የሚያሳየው የፖለቲካ ምህዳሩን ለመድፈን ያላቸውን አስተሳሰብ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም፡፡

ከመሰረታዊ ሃሳብ ወደ ተቃዋሚዎች ጎራ ልውሰዳችሁና ፓርቲዎቹ ጎራ ውስጥ ያሉ ብዙ አሳዛኝ ጉዳዮችን ደብቀው መዝለቅ የሚችሉበት ሁኔታ የለም፡፡ባለፉት ዓመታት የፖለቲካ ሂደቱ በየጊዜው እያረጋገጠ የመጣው እውነታ፤ በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጥያቄን በተመለከተ የተቃዋሚዎች ጎራ የችግር ምንጭ እንጂ የመፍትሄው አካል መሆን ያቃታቸው መሆኑን ነው፡፡

ፓርቲዎቹ በመሰረታዊ የጋራ ጥቅም ተመስርተው አይደሉም ጥምረት የሚፈጥሩ፡፡በያንዳንዱ የተቃዋሚ ፓርቲ መሰረታዊ የሆኑ የመርህ ልዩነት እያለ ሳይስማሙና ሳይግባቡ ነው ጥምረት የሚፈጥሩት፡፡ትንሽ ቆይተው ደግሞ ይበታተናሉ፡፡አንዳንዴማ ጥምረት መቼ እንደፈጠሩ ሳንሰማ መበታተናቸው ቀድመን የምንሰማበት አጋጣሚ አለ፡፡ጥምረት ሲፈጥሩ በጋራ ጥቅም ላይ ተመስርተው ሳይሆን አንዱን የበላይ ሌላኛውም የበታች በማድረግ ነው፡፡ይህ ደግሞ በውስጣቸው ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ያጠበዋል ፡፡ውስጣቸው ዴሞክራሲያዊ አይደለምና!

ስለሆነም ትናንት ጥምረት ፈጥረናል የሚሉን የነበሩ ፓርቲዎች በጎራቸው ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ስላጠበቡት ጭራሽም ስለደፈኑት አሁን ተበታትነው ስለአገራቸው መጪውን ተስፋ ከማውራት ይልቅ ራሳቸው በራሳቸው ሲሰዳደቡና እንካ ሰላምታ ሲባባሉ እያስተዋልን ነው፡፡አሁንማ ከዛ አልፎ ከህዝባችን በላይ የሚያከብሯቸውና የሚሰግዱላቸው የውጭ ዜጎች ሲሰበስቧቸው እኔ ከእገሌ የተባለ ተቃዋሚ ድርጅት ጋር አልወያይም፤እሱም በተገኘበት አልገኝም በማለት ሲደስኩሩ ይታያሉ፡፡እዚህ ላይ ኢምባሲዎች ብቻየን ነው የምወያየው ያለውን ፓርቲ ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ አካሄድ እየሄደ እንዳለ ሳይገነዘቡ አልፏል ብዬ አላምንም፡፡በመግቢያዬ እንደገለፅኩት ብቻዬን ልወያይ ያለውን ፓርቲ አንድ ዓይኑን ሲያጠፋ ፍላጎቱ ግን ለሌላውን ተቀኛቃኙ ፓርቲ ሁለት ዓይኑን ለማጥፋት በማሰብ ነው፡፡ይሄ ደግሞ ፓርቲዎች በውስጣቸው የተዳፈነ የፖለቲካ ምህዳር እንዳለ የሚያሳይ ነው፡፡ለአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት አጋር መሆን ሲገባቸው እኔ ጠንካራ ሆኜ ሌላውንም ከሚጠነክር እኔ ተዳክሜ ሌላውን ክፉኛ ቢዳከም እመርጣለሁ የሚል የተቃዋሞዎች አስተሳሰብ ለነርሱም፤ ለህዘባችንም ለአገራችንም የዴሞክራሲ ሂደት አይጠቅምምና ራሳቸውን ቢፈትሹ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

መንግስት ዋነኛውና ወሳኙ መብት እስከ መገንጠል በሕገ መንግስቱ በተረጋገጠበት መሰረት ተግባራዊ አድርጎ ከመንቀሳቀስ ባሻገር ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ወሳኝ ናቸው ብሎ ያመነባቸው የተለያዩ ሕጎች አውጥቷል፡፡ ከመጀመርያ ሲነሳ እስክ መገንጠል የሚደርስ ያልተገደበ  መብት በሕገመንግስቱ መሰረት የተቀበለና  የፖለቲካ ምህዳሩን ያሰፋ መንግስት የተለያዩ ሕጎች በማውጣት የፖለቲካ መድረኩ ያጠበዋል የሚል እምነት የለኝም፡፡ከመጀመርያም ባህሪው ስላልሆነ፡፡የአገሬ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች ግን በመካከላቸው ያለውን የፖለቲካ ምህዳር ሳይገመግሙና ሳያስተካክሉ ስለ አገራችን የፖለቲካ ምህዳር የመገምገም ብቃት ያላቸው አይመስለኝም፡፡አበቃሁ!